# የዒድ አከባበር ደንቦች

## በጣሀ አህመድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ለአለማት ጌታ ለአላህ የተገባ ነው፡፡ የአላህ ሰላትና ሰላም በመልእክተኛው ሙሀመድ፤ በቤተሰቦቻቸው እና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን፡፡

# ኢስላም በራሱ የተሟላ ነው

እንደሚታወቀው ዲናችን (ሀይማኖታችን) ኢስላም ምሉዕ ነው፡፡ ስለሆነም ለሁሉም የአምልኮ ዘርፎች እንዲሁም የህይወት መስኮች ደንቦችን ደንግጓል ስርዐቶችንም አስቀምጧል፡፡ ሕግጋቶቹ ፍትህዊ እና ሚዛናዊ ስርዐቶቹም ለሁሉም ቦታ እና ዘመን የሚበጁ ናቸው፡፡ አላህ (ሱብሀነሁ ወተአላ) እንዲህ ይላል፡፡

{الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا} المائدة 3

**‹‹ዛሬ ሐይማኖታችሁን ሞላሁላችሁ፤ ፀጋዬንም በእናንተ ላይ ፈፀምኩ፤ከሀይማኖት በኩልም ለእናንተም ኢስላምን ወደድኩ....››** (አልማኢዳ፡ 3)

ከዚህም በመነሳት መጨመርንም ይሁን መቀነስን አይቀበልም እንዲሁም ከሌሎች መኮረጅንም ሆነ መመሳሰልን ይከለክላል፡፡

ይህንን እዉነታ የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላምና ሰላት በርሳቸው ላይ ይሁን) በነዚህ ሁለት ነብያዊ አስተምህሮቶች ይገልፁታል፡፡

**ففي حديث عائشة رضي الله عنها أنها قالت : قال رسول الله صلى الله عليه وسلم : ( من أحدث في أمرنا هذا ما ليس منه فهو رد )** رواه البخاري (2697) ومسلم (1718)

**‹‹በዚህ በዲናችን ላይ ከርሱ ያልሆንን ያመጣ (ሰው) ስራው ተመላሽ ነው። (ተቀባይነት አይኖረውም)››** (ቡኻሪ እና ሙስሊም ዘግበውታል)

**عَنْ ابْنِ عُمَرَ قَالَ : قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ : ( مَنْ تَشَبَّهَ بِقَوْمٍ فَهُوَ مِنْهُمْ ) رواه أبو داود (4031)**

**‹‹ከህዝቦች የተመሳሰለ እረሱ ከነርሱ ነው።››** (አቡ ዳውድ ዘግበውታል)

# ዒድ ማለት ምን ማለት ነው?

ኢብኑል ዓረቢዕ ‹‹ዒድ›› (ዒድ) ብሎ ስለመሰየሙ ሲናገሩ በየአመቱ አዲስ ደስታን ይዞ የሚመለስ ከመሆኑ አንፃር መሆኑን እና ‹‹ዓደ›› (ተመለሰ) ከሚለው ቃል የተወሰደ መሆኑን ይገልፃሉ። እዚህ ላይ ልብ ልንልን የሚገባው (ዒድ) ቂያማ እስቂቆም ተመላልሶ የሚመጣ ቢሆንም እኛ ግን የሚቀጥለውን ለመድረስ ምንም ዋስትና እንደሌለን ነው። ስለሆነም ከአላህ ህግ ፈፅሞ ልንወጣ አይገባም።

عَنْ أَنَسٍ-رضي الله عنه- قَالَ: قَدِمَ رَسُولُ اللَّهِ -صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ- الْمَدِينَةَ ، وَلَهُمْ يَوْمَانِ يَلْعَبُونَ فِيهِمَا فَقَالَ:(مَا هَذَانِ الْيَوْمَانِ؟) قَالُوا: كُنَّا نَلْعَبُ فِيهِمَا فِي الْجَاهِلِيَّةِ، فَقَالَ رَسُولُ اللَّهِ -صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ-: (إِنَّ اللَّهَ قَدْ أَبْدَلَكُمْ بِهِمَا خَيْرًا مِنْهُمَا يَوْمَ الْأَضْحَى وَيَوْمَ الْفِطْرِ) رواه أبو داود

አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዲህ ይላሉ **‹‹የአላህ መልእክተኛ (ሰላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) መዲና ከተማ ሲመጡ የመዲና ሰዎች በመሀይምነት ዘመን (ደስታቸውን የሚገልፁባቸው) የሚጫወቱባቸው ሁለት ክብረበዓላት ነበሩዋቸው። ይህንን ባዩ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ። በእነዚህ በሁለቱ ምትክ ከእነርሱ በተሸሉ ሁለት ክብረበዓላትን ቀየረላችሁ፤ እነሱም የፈጥር እና የአድሀ በዓላት ናቸው።››**

(አቡዳውድ እና አህመድ እንደዘገቡት)

ከዚህ ሀዲስ ጋር በተያያዘ ኡለማዎች የተረዱቸዉን ሁለት ቁም ነገር ልናስተውል ይገባል።

አንደኛ ፦ **ከሌሎች (ከእስልምና ውጭ) ካሉ ማህበረሰቦች ጋር መመሳሰል የተከለከለ መሆኑ እና፤**

ሁለተኛ ፦ በኢስላም የተደነገጉ ክብረ በአላት ሁለት ብቻ መሆናቸውን ነው ።

# ከዒድ ዋዜማ ጀምሮ ልንፈፅማቸው የሚገቡ ነገሮች

ከዚህ በላይ በአጭሩ ዒድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲሁም በኢስላም የተደነገጉ ክብረ በአላት ኢድ-አልፈጥር እና ኢድ-አልአድሀ ብቻ መሆናቸውን ከተረዳን፤ በእነዚህ ሁለት ዒዶች ዋዜማ እና በእለቱ ምን ማድረግ ይወደዳል? ምንስ ይፈቀዳል? ምን ከማድረግ ልንከለከል ይገባል? ወደ ሚሉት ነጥቦች እንምጣ።

በመጀመሪያ ከዒድ ዋዜማ ጀምሮ ልንፈፅማቸው ከሚያስፈልጉ ነገሮች ስንነሳ፤

1. በኢደል-ፊጥር ዒድ መሆኑ ከተረጋገጠበት ሰዐት አንስቶ ሰላቱ እስኪጀመር በኢደል-አድሀ ደግሞ ከዙል ሂጃ የዘጠነኛው እለት ፈጅር ሰላት አንስቶ የአስራ ሶስተኛው እለት ፀሀይ እስከምትጠልቅ ድረስ **ተክቢራን** ማድረግ ይገባል።
2. **መታጠብ** እራስን ማስማመር እና ከልብሶች መካከል የተሸለውን እና ቆንጆውን መልበስ ከሰለፎች የተዘገበ ተግባር ነው።
3. ሴቶችን በተመለከተ በዚህ እለትም ይሁን በሌላ ጊዜ ከቤታቸው እንዴት መውጣት እንዳባቸው በሸሪዐ የታወቀ ነው። እናም ከመገላለጥ እና ሽታ ያላቸውን ነገሮች ተጠቅመው ከመውጣት ተቆጥበዉ ከቤታቸው ወደ መስጊድ ወይም ወደ ዒድ መስገጃ ስፍራ ሊሄዱ ይገባል።

የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) ለጋብቻ የቀረቡና የደረሱ እንዲሁም በወር አበባ ላይ ያሉ ሴቶችን ጨምሮ ወደ ዒድ ሰላት መስገጃ ቦታ ስፍራ እንዲወጡ ትዕዛዝ ማስተላለፋቸውን ተከትሎ እንዲህ የሚል ጥያቄ ተጠይቀው ነበር **‹‹እንዳችን ጅልባብ ባይኖራት ምን ታድርግ?››** እሳቸውም እንዲህ አሉ **‹‹እህቷ (ጓደኛዋን) ታውሳት››**

(ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

عَنْ زَيْدِ بْنِ خَالِدٍ الْجُهَنِيِّ، قَالَ : قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ : **" لا تَمْنَعُوا إِمَاءَ اللَّهِ مَسَاجِدَ اللَّهِ ، وَلْيَخْرُجْنَ تَفِلاتٍ "** رواه أحمد وأبو داود وصححه الألباني

በሌላውም ሀዲስ እንዲህ ብለዋል **‹‹ሴቶችን መስጊድ ከመሄድ አትከልክሏቸው ነገር ግን ከቤታቸው ሽታ ያለው ነገርን ተጠቅመው እንዳይወጡ።››**

(አል-ኢማም አህመድና አቡዳውድ ሲዘግቡት አልባኒ ሰሂህ ብለውታል)

4. በዒደል ፊጥር ሰጋጁ ወደ መስገጃው ከመውጣቱ በፊት ዊትር (አንድ፤ ሶስት፤ አምስት .....) ቁጥር ያላቸውን ተምሮች በልቶ መውጣት

5. ለኢድ ሰላት ከመውጣት በፊት ዘካተል-ፊጥርን ለተገቢው ወገን መስጠት

6. ሰላተል ኢድን ለመስገድ ከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት ሊኖር ይገባል። ምክንያቱም ይህ ተግባር ከታላላቅ የኢስላም መገለጫዎች አንዱ ከመሆኑም ባሻገር የአላህ መልእክተኛ (ሰላትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁንና) ሰላተል ዒድ ከተደነገገበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሕልፈታቸው ትተውት አያውቁም በተጨማሪም በመሰረቱ መስገድን የተከለከሉትን የወር አበባ ላይ ያሉ ሴቶች ሳይቀር በቦታው ላይ እንዲገኙ አዋዘል።

7. ሰላቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በተቻለ አቅም ኹጥባን ማዳመጥ

8. ወደ ዒድ ሰላት ከሄዱበት መንገድ በሌላ መመለስ

9. የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት መለዋወጥ። ይህም ‹‹**ተቀበለላሁ ሚና ወሚንኩም**›› የሚል ሲሆን የተለያዩ የኢስላም ሊቃውንት ከሰሃቦች መገኘቱን አረጋግጠዋል።

10. ከኢድ ጋር በተያያዘ ዘካተል ፊጥርን መስጠት መታዘዙ የተለያዩ ችግረኞችን ማስታወስ እና አቅም በፈቀደ መጠን ችግራቸውን ለመቅረፍ ጥረት ማድረ የሚደገፍ ተግባር መሆኑን የሚያመለክት ነው።

11. በአጠቃላይ ሸሪዐው ያዘዘባቸውን እና የፈቀዳቸውን ተግባራት በፈፀም የሚፈቀድና የሚወደድ ይሆናል

# የተክቢራ አፈፃፀም

1. ከመልክተኛው ትክክለኛ ሰነድን መሰረት ያደረገ እና የተክቢራን አባባል ዝርዝር ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ ባይገኝም ከሰሀቦቻቸው ግን ‹‹**አላሁ አክበር አላሁ አክበር ወሊላሂልሀምድ**›› እና የመሳሰሉት አባባሎች በትክክለኛ ሰለድ ተዘግበዋል። ስለሆነም ሙስሊሞች እነዚህን አባባሎች የትኞቹ እንደሆኑ ማጥናትና እነርሱን ማዘውተር ይጠበቅባቸዋል። ኢብኑ ሀጀር አል-አስቀላኒ ፈትሁል ባሪ በተሰኘው ኪታባቸው እንዲህ ይላሉ ‹‹**በዚህ ዘመን (ተክራን በተመለከተ) ብዙ መሰረት የሌላቸው ጭማሪዎች ተከስተዋል።**›› ይህ በሂጅራ አቆጣጠር ከ773-852 የኖሩት የኢስላም ሊቅ ንግግር ነው። ታዲያ ባለንበት ዘመን ምን ያህል ጭማሪ ተከስቶ ሊሆን እንሚችል ስናስተውል በጉዳዩ ላይ ከባድ ጥንቃቄ ልናደርግ እንደሚገባ ያመላክተናል።
2. በአንድ ድምፅ ወይም አንድን ሰው የአዝማች አውጪ ሌላውን ተቀባይ ሆኖ የሚደረግ ተክቢራም ሱናን የሚቃረን ተግባር ነው።

በዚህ ዙሪያ እንደ መረጃ የሚጠቀሰው የዑመር ተግባር የሚያመለክተው ሚና ላይ በድንኳን ውስጥ ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተክቢራ ሲያደርግ ሰዎችም ተክቢውን ሰምተው ተክቢራን ማድረግ እንዳለባቸው በማስታወስ እነርሱም ተክቢራ ያደርጉ እንደነበረ እንጂ ሌላ አይደለም። የህ ክስተት፤ በጋራ ድምፅ እርሱን እንደ አዝማች እነርሱ እንደ ተቀባይ ሆነው ይቀጥሉ ነበር የሚለው እንድምታ አያስጨብጥም ሲሉ ኡለማዎች ይናገራሉ።

# ጥቂት ከዒድ ጋር በተያዘ የሚፈፀሙ ስህተቶች

1.ዒድ መሆኑ ከታወቀበት ሰአት ጀምሮ ወንዶች ከሰላተል ጀመዓ መቅረት ብሎም በረመዳን ሲሰግዱት የነበረውን ዊትር ሰላት መተው፤ አንዳንዴም አምልኮዎች በዚህ ያበቃሉ የተባለ ይመስል እርግፍ አድርጎ መተው።

2.የኢዱን ዋዜማ ሌሊት በተለያዩ ዒባዳዎች ህያው ማድረግን በተመለከተ የመጡት ሀዲሶች ከሰነድ አንፃር ደካማዎች ናቸው። ነገር ግን ሊሊቱን በተለያዩ ነገሮች ማሳለፍ፤ በዚህም የተነሳ የፈጅር ሰላትን አለመስገድ እና ሰላተል ኢድን እንደ ቀላል በመመልከት ችላ ብሎ መተው። **«ሰላተል ኢድ በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ በነፍስ ወከፍ ግዴታ ነው»** የሚለው የአቡ ሀኒፋ እና የኢማሙ ሻፊዒይ አቋም ነው። ከኢማሙ አህመድ ከተዘገቡት ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች አንዱ የሚጠቁመው ይህንኑ አቋም ነው። ሸይሁል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ እና በዙ ኡለማዎችም ይህ አቋማቸው መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

3.በአለባበስና መቆነጃጀት ዙሪያ ከሚከሰቱ ስህተቶች መካከል በአብዛኛው ወንዶች ፂማቸውን በመላጨትና በማሳጠር እንዲሁም ልብሳቸውን ከቁርጭምጭሚታቸው በታች እነዲወርድ በማድረግ የሚፈፅሙት ስህተት ይገኝበታ።

ሴቶች ደግሞ ሽቶን በመቀባት በመገላለጥ የሚፈፅሙት ስህተትም አደገኛ ነው። እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ የመጡት ነብያዊ አስተምህሮቶች እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ ናቸው።

عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ عَنْ النَّبِيِّ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ : ( مَا أَسْفَلَ مِنْ الْكَعْبَيْنِ مِنْ الْإِزَارِ فَفِي النَّارِ) رواه البخاري (5787)

ከአቡሁረይራ በተላለፈ ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል ‹‹ከሽርጥ ከቁርጭምጭሚት የወረደዉ የእሳት ነው››

(ቡኻሪና በቁጥር 5787 ዘግበዉታል)

ይህ ሁሉንም ልብስ እንደሚያካትት ለመግለፅ አል-ኢማም አልቡኻሪይ "ከቁርጭምጭሚት የወረደዉ የእሳት ነው›› የሚል ርዕስ ሰጥተዉታል።

‹‹ማንኛዋም ሴት ሽቶን ተነስንሳ ወደ መስጂድ የወጣች እንደሆነ እስክጣጠብ ድረስ ሰላቷ ተቀባይነት የለውም።››

(ኢብኑ ማጃህ እና አህመድ ዘግበውታል አልባኒም ሰሂህ መሆኑን ገልፀዋል።)

عن أبي هريرة قا ل: قال صلى الله عليه وسلم : "صِنفانِ مِن أهلِ النارِ لم أرَهما: قومٌ معهم سِياطٌ كأذنابِ البقرِ يَضْرِبُونَ بها الناسَ، ونِساءٌ كاسياتٌ عارياتٌ مميلاتٌ مائلاتٌ، رؤوسُهُنَّ كأسنِمَةِ البُخْتِ المائلةِ لا يَدْخُلْنَ الجنةَ ولا يَجِدْنَ رِيحَهَا، وإن رِيحَهَا لَيوجَدُ مِن مَسيرةِ كذا وكذا" .
رواه مسلم (2128)

‹‹ከእሳት ሰዎች መካከል ሁለት አይነት ሰዎች እኔ ያላየኋቸውም(ወደፊት የሚመጡ)፤ ለብሰው ያልለበሱ አካሄዳቸው እና እንቅስቃሲያቸው ወደርካሽ አላማ ያዘነበሉ፤ ሌሎችንም የሚያሳስቱ ፀጉራቸው ልክ እንደ ግመል ሻኛ የተከመረ ሴቶች ናቸው፤ እንደነዚህ አይነቶቹ ጀነትን አይገቡም ሽታዋንም አያገኙትም።›› (ሙስሊም ዘግበውታል)

4.ባዕድ በሆኑ ወንዶችና ሴቶች መካከል መቀላቀል፤ አልፎም መጨባበጥና መሳሳም። ይህ ሸሪዐው ክፉኛ የኮነነው ተግባር ነው፤ የአላህ መልእክተኛ (ሰላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) ከእለታት አንድ ቀን ከመስጂድ በመውጣት ላይ ሳሉ ወንዶች ከሴቶች ጋር በመንገድ ላይ ተቀላቅለው ተመለከቱ ይህንን ክስተት በማስመልከትም **‹‹ከወንዶች ወደ ኋላ ሁኑ፤ የመንገዱንም መሀከል ይዛችሁ ልትጓዙ አይገባም››** አሉ። ይህንን ሀዲስ የዘገበው ሰሀቢ.ይ **‹‹ከዚህ በኋላ ሴቶች በጣም ወደ ዳር ከመውጣታቸው ልብሳቸው በአጥር ይያዝ ነበር።››** በማለት ይናገራል።

(አቡዳውድ ሱነናቸው ላይ ሲዘግቡት አልባኒ ሀሰን የሚል ደረጃ ሰጥተውታል)

ይህ ሀዲስ ሸሪዐ በጥቅሉ ወደ ሀራም የሚያደርሱ ነገሮችን የከለከለ መሆኑን ከሚያሳዩ መረጃዎች አንዱ ነው።

በሌላ ሀዲስ ላይ የአላህ መልእክተኛ (ሰላትና ሰለም በርሳቸው ላይ ይሁን) **‹‹እኔ ሴቶችን አልጨብጥም››** ማለታቸው ሰፍሯል። ሀዲሱ አንድ ሰው ምንም እንኳ የተቀደሰ አላማና ንፁህ ልቦና ነው የያዝኩት ቢልም ባዕድ ሴቶችን ከመጨበጥ ሊቆጠብ እንደሚገባ የሚያመለክት ነው።

5. እንደ ሙዚቃ እና መሰል የተከለከሉ ነገሮችን በማድጥ እንዲሁም የሴቶች ፊልሞችን መመልከት እና ጊዜን ማጥፋት። ሌሎችንም እርም የሆኑ ተግባራት መጠንቀቅ ይገባል

6.ምግብና መጠጥን ማባከን።

# ዓድ ጁምዓ(ዓርብ) ዕለት ከዋለ

**የሳዉዲ ዓረብያ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ በቁጥር 21160 ካወጣው መግለጫ ተከታዮቹን ሀሳቦች ጠቅሷል።**

- ኢማሙ ሰላተል ጁምዓ እንዲሰገድ የማድረግ ግዴታ አለበት። ጁምዓ ለመስገድ በቂ ሰዉ ካልተገኘ ዙህርን ያሰግዳል።
- ሰላተል ዒድ የሰገደ ሰው የጁምዓ ሰላትን ባይገኝ ይፈቀድለታል። ዙህርን በወቅቱ ይሰግዳል። ሆኖም ግን ከሙስሊም ወንድሞቹ ጋር ጁምዓን ቢሰግድ የተሻለ ነው።
- የዒድን ሰላት ያልሰገደ ግን ይህ ፍቃድ አይመለከተዉም። ጁምዓን የመስገድ ግዴታ አለበት።
- በዚህ እለት ጁምዓ በሚሰገድባቸዉ መስጂዶች ሲቀር የዙህር አዛን አይደረግም።